ፍኖተ ዴሞክራሲ የኢትዮጵያ አንድነት ድምጽ

Finote Democracy Voice of Ethiopian Unity

Efdpu@aol.com www.Finote.org

በፍኖተ ዴሞክራሲ የኢትዮጵያ አንድነት ራዲዮ
በጥር 7 ቀን 2011 ዓም የተላለፈ ሐተታ

# ሀገርን ሊያጠፉ ያሉ ስህተቶች

ለነገሩ ትልቁ ስህተት የሆነብን ራሱን ጠቅላይ ሚኒስቴር ብሎ ያሾመው ነው ። አሜሪካና አረቦች በጠነሰሱት ሴራ ሕዝባዊ የጋራ ትግላችን ተደናቅፎ በረቀቀ ስልት ሹምን ሲያመጡብንና፤ ብዙዊችን ሲያደናግሩ ያ በመጀመሪያ ደረጃ ቃል ነበር እንደተባለው ዋናውምና አቢዩ ስህተታችን ነበር ። ሹሙን ሰይመውብናና አግዘውት ወያኔ ኢሕ አዴግን አሰቀጥላለሁ ብሎ፤ የሕዝብን የሽግግር ሂደት ፍላጎት አደንቅፎ'ለኢትዮጵያ አንድነት ጠላቶች ሁሉ ሀገራችንን በርግዶ ሰጥቶ፤ግድያና ሽብርን አስፋፍቶ በደመ ነፍስ ገዛሁ ሲል እነሆ ኢትዮጵያን በጥፋት ኮረብታ ላይ አድርሷታል ። የመጀመሪያውና አቢዩ የተፈጸምብን ስህተት እንበለው ።

ሌላው ዋና የተፈጸመብን በደል ወይም ራሳችንን ሰለባ ያደረግንለት ስህተት ሹሙ ኢሕአዴግን አስቀጥላለሁ፤የመለስን ልማታዊ ዝባዝንኬ ይዤ እጓዛለሁ፤ሽግግር ሳይሆን በኢሕአዴግ ስር ምርጫ ይደረጋል ብሎ ሲነሳ በጭብጨባ መቀበላችን ነው ። እያንዳንዱ ሕዝብ የሚያገኘው መንግሥት ወይም አገዛዝ የሚገባውን ነው ማለት ባንፈልግም የሕዝብ ሀላፊነት ደግሞ በቀላሉ የሚታይ አይደለም ።ከሹሙ አልፎ ለጻረ ኢትዮጵያው ሻዕቢያ የተደረገለት አቀባበል አሳዛኝ ነው ። በቅስቀሳና ግዴታ ሕዝብን አሰልፎ ማውጣት ያለና የማናውቀው ቢሆንም ሻዕቢያን ለመቀበል የወጣው ሕዝብ፤ወያኔን ደግፎ የተሰለፈው የትግራይ ሕዝብ ፤ዳውድ ኢብሳና ኦነግን የተቀበለውና የገንጣዮችን ባንዲራ ያውለበለበው እንዲሁ በለሆሳስ የሚታለፍ አይደለም ። ኢትዮጵያዊ ግዴታን የዘነጋ ነው ወይም ለሚያስገዱት የተኅነበሰ ነው ማለትም እንችላለን። ድክመታችን ስህተታችንም ይህም ነው ። ተክለሰውነትን በማቀፍና ሰውየውን አምላክ የሰጠን ነው ብሎ ከንቱ ውዳሴ በመደርደር፤ ለመሞኘት በመጨፈን ሀገርን መጉዳታችንን መገንዘብና መታረም ይጠበቅብናል ። 27 ዓመት የወያኔ ኮለኔልና ሹም የሆነ ግለሰብ- ለኢትዮጵያ ውስብስብ ችግር በግሉ ወይም በቡድኑ መፍትሔ ሰጪ ይሆናል ብሎ መገመት ስህተት ለመሆኑ ምንም እሰጥ አገባ አያሻውም ። መነጋገር ካለብን በዚህ ላይ ነው ። ሹሙ ማንም ሳይመርጠው እንዴት ተሰየምብን ? ሂደቱንስ ሕዝባዊ ነው ወያኔያዊ ? ወይስ የአሜሪካ? ከመነሻው የሹሙ አመጣጥ ሀገርን የሚጎዳ ስህተት በመሆኑ--የሕዝብን ትግል ለማቅስቆም የሆነ በመሆኑ--ይህ መሰረታዊ ጉዳት በሽግግር ሂደት ታርሞ ወደ መፍትሔ ካልተኬደ ቢወቅጡት እምቦጭ እየሆነብን ያለው ለዚህ ነው ። ዓይናችን እያየና እየተናገርነው ወደከፉ አዘቅት እየወደቅንም ነው ። በተጀመረው አሜሪካናዊ ሂደት ሀገራችን ከጥፋት አናድንድም ። ዘበት ነው ። ሹሙ የአሜሪካና የነሳውዲን ጥቅምና ዕዝ አስቀድሞ እስካለ ድረስ ለኢትዮጵያ ምንም አይጠቅምም--ይጎዳል እንጂ ።

ሕዝብ ደሙን የገበረው የራሱ ሕዝባዊ መንግሥት እውን እንዲሆን እንጂ አምባገነን በሌላ ፈላጭ ቆራጭ፤ዘረኛ በሌላ ዘረኛ እንዲተካበት አይደለም ። ቹሙ ትግልን አስቆመ አኮላሸ እንጂ አላስቀጠለም፤የስር ዓት ቀጣይነትን ለማረጋገጥ ደፋ ቀና አለ እንጂ ለውጥን አላመጣም ። ዘንዶው ሄድ ሲል አዞው መጣብን ነው--ሁሉም ጥርሱን አግጦ ሕዝብን ሊበድል፤ሊበዘብዝ ። ግደይ በገመቹ መተካቱ ልሕዝብም ለሀገርም የሚበጅ ለውጥና መሻሻል ካለመሆኑ ባሻገር እንዲይውም ጻረ ሀገርን ቀውስ እያባባሰ እንደሚገኝ ይኸው ዓመት ሳይሞላ እያየነው ነው ። በግሉ ይሾማል -ያውም ሕዝብ የጠላቸውን ወንጀለኞች ።

ሹመቱ ብሄር ብሄረሰብና ብቻ ሳይሆን ሀይማኖትንም የሚከተል መሆኑንም አይተናል ። የፖለቲካ እስረኞች አሁንም እንደማቀቁ ናቸው--በተለይ በትግራይ እስር ቤቶች ። የይስሙላና አደናጋሪ ለውጦችን ሲያስትቃፉን መሠረታዊውን ለውጥ እምቢኝ ብለውናል ።ባያስገርምም የሚያሳዝነው ደግሞ የሕዝብ ወገን ነን ሲሉ የነበሩት ሁሉ በአገዛዙ ስር ወድቀው ፤ ተቃዋሚ ሳይሆን አጃቢ፤ ተፎካካሪ ሳይሆን ተለጣፊ ሆነው፤ የሕዝብንም መፈክር ትተውና አርክሰው መገኘታቸው ነው ። ያ ወያኒን ያርበተበተ ኢትዮጵያዊነት ተሸረሸረ፤የጠባቦች መንጋ በሀገራችን ፈነጨ፤የሕዝብ የጋራ ሰንደቅ ተጥሎ የክፍፍል ባንዲራዎች ተውለበለቡ።በዚህ ሁሉ ጫጫታና ሂደት ሹሙ የተጠኑና የማይጨበጡ ቃላትን እየደረደረና እያስጨበጨበ፤ እያየነው ኢትዮጵያን ለአደጋ ጥሏል ። በግራ አመራርና በነጻ ምርጫ ምደባ--በችሎታ --ብናምንም ሹሙ ይምራ እንኳን ቢባልም ሊመራ ከቶም አልተቻለውም ።አድርባዮች የሌለውን ችሎታ ሰጥተው ጮቤ ቢረግጡም ሰውየው እንዳልቻለበትና የሕዝብን መብት ማክበርንም እንዳልፈለገና ዋናው ዓላማው ሊነግስብን ብቻ መሆኑን ማወቅ አልተሳነንም ። እግረ መንገዳችንን ግን ማን በሀቅ ኢትዮጵያዊ ማን አድርባይና ጠላት እንደሆነ በሰፊው ለማወቅ ችለናል ።

ስህተታችን በግርግር ትግላችን መደናቀፉ ነው ። ኢትዮጵያዊነት መሸርሸሩና ጠባቦች የበላይነትን ማግኘታቸው ነው ።ስር ዓቱ ላይ ያነጣጠረ ትግል ሳይሆን የርስ በርስ ፍጅቱ ተፋፍሟል ። በወያኔና ሌሎችም አራጋቢነት። የሽግግር ሂደት የሚለው ተትቶ በወያኔ ህግና ምርጫ ተብዬ አያስቅ ቧልት ውስጥ ለመዘፈቅ ሁሉም ዝግጁ ሆኖ ይገኛል ። ኢትዮጵያዊ መፈክርን ይዞ እንኳን እንዳይወዳደር የክልል ሽንሽናው ጦፎ የአትድረሱብን ባዮች ዘመን መጥቷል ። ሁሉም በየክልሉ የበላይነትን ለመያዝ ሲፈራገጥ ሀገር ተረስታለች፤ተከፋፍላለች፤ለውድቀትም ተዳርጋለች ።ሹሙ ያቀፉቸውና ያስተናገዳቸው ጸረ ኢትዮጵያ የሆኑ ሁሉ ስራቸው ያው ማፍረስ እንጂ ፤ጦርነት ና ግድያን ማፋፋም እንጂ መገንባትና ሰላምን ማስፈን አይደለም ። ይህ እንደሚሆን ብንናገርም የጠፋው ሰሚ ነው ። የዚህ ሂደት ቁንጮዎች ደግሞ በመቀሌ የመሸጉትና ቤት መንግሥት ገባን ያሉት ናቸው ።ምስጢር የለውም ።የሹሙ እቅድና ዓላማ ኢትዮጵያዊ ሳይሆን ብሄር ጠቀስና ሀይማኖታዊ ነው ። ስህተታችን፤ በጊዜ ነቅተንባቸው ሳይፈነጩብን ልናቆማቸው በህብረት አለመጣራችንና ለአስመሳዮችና ጠብቦች ተሸናፊ ህነን መገኘታችን ነው ።የጀመርነውን የትግል ጉዞ በነበረው ኢትዮጵያዎ መንፈስ ቀጥለን ስር ነቀል ለውጥን ለማምጣት ብንቀጥል ኖሮ ዛሬ በገባንበት ማጥ ባልተገኘን ነበር ። እነ አሜሪካ ንቀውን ሲጫወቱብን ፤ትላንት ኮሽን ዛሬ ደግሞ ያማሞቶ ሿሚ ሽላሚ ባልሆኑብን ነበር ። ባለቤቱ ያቀለለውን አሞሌ እንዲሉ ሆኗልና ጥፋቱና ድክመቱን ወደ ራሳችን ማዞር ተገደናል ።

አንጎል የተፈጠረው ለመርሻ አይደለም ። መርሳትን ነው መርሳት የተባለውን መቸም መዘንጋት የለብንም ። ትላንት ስንቱን ወነጀል በሕዝብና በሀገር ላይ የፈጸሙት ጀግና ነጻ አውጪ ተብለው ሲምገሱና ለሀገር የተዋደቁት ሲረሱ ሲገለሉ ማየት ልማድ የሆነብን ይመስላል ።ከፉ ስህተት። እነ በላይ ዘለቀን ሰቅለው፤እነ መንግስቱና ገርማሜ ንዋይን ገድለው ባንዳን የሚሾም ስር ዓት ሰፍኖብን ቆይቶ ስለነበር ለጉዳዩ እንግዳ አይደለንም ። ያጀበን ምጸት ነበርና፤ ነውናም። ዛሬም ከሹሙ ዙሪያ እነማን አሉ ?እነ ማን ናቸው እየተሾሙና የክብር እንግዳ እየተባሉ ያሉት ? እሱ ራሱስ ማን ነው ፤የት ነበር፤ማን ከዚህ አደረሰው ?ታሪኩን የረሳ ሕዝብ ነጋ ጠባ ለጭቆና ቢዳረግ የሚገርም አይሆንም ። የባድሜውን ወራሪ የናቅፋው ጀግና ብሎ ከወሰደም ለሚከተልበት ሁሉ ሀላፊ ራሱ ነው ። ስህተትና ድክመትን በነቂስ አውጥቶ፤ደፍሮ ለማረም መነሳት ዋናው መንገድና መፍትሔ ነው ። የወያኔ ኢህ አዴግ ስር ዓት መፍረስ አለበት ። መታደስ ሳይሆን መወገድ ። ይህ ግባችን ነውና ከዚህ ላነሰ መፍትሔ ጆሮም መስጠት የለብንም ማለት ነው ። ከዚህ አንጻር ሹሙና ጓደኞቹ በትግላችን ላይ ደንቃራ እንደሆኑ መገንዘብ እንችላለን ። የሽግግር ሂደት መጀመር፤ ነጻ መርማሪ ቦርዶችን ማቋቋም፤አድልዎና ዘረኝነትና ማስወግድ

ማገድ፤ጠባቦችን መቆጣጠርና በጋራና ዴሞክራሲያዊ ውይይትና ስምምነት ሂደት ሕዝብ የሀገሩ ባለቤት እንዲሆን ማድረግ ያዋጣል ። የተያዘው ጉዞ የውድቀት ነው ። የግል ስልጣን ፈላጊዎሽ የቅዠት ጉዞ ነው ።ቃላት ቢቀባባ አስቀያሚ ከመሆን ሊድን ያልቻለ ።የውድቀት ጉዞ፤ጸረ ኢትዮጵያ ሂደት ።

ጸረ ወያኔ ጸረ ኢሕአዴግ ትግላችን ይፋፋም!

ኢትዮጵያዊነት ያቸንፋል !!